የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ

ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

<u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

1. በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000021168355 ሰኔ 30/2009 በቀረበው የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ የሚታይ ብር 6,627,408.44 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

2. በድምሩ ብር 30,426.21 የኒቨርሲቲውን ለለቀቁ እና በብልጫ አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፣
3. በውጭ አገር ጉዞ የውሎ አበል የክፍያ ተመን መሠረት ክፍያ መፈፀም ሲገባው ከመመሪያው ውጭ በመከፈሉ ብር 33,715.05 በብልጫ ወጪ መደረጉን፣
4. ለ3ኛው ሀገር አቀፍ የምርምር ጉባኤ የወረቀት ጽሁፍ ላቀረቡ ለእያንዳዳቸው ከብር 2,500.00 እስከ 5,000.00 በድምሩ ብር 95,900.00 ከመመሪያ ውጭ አለአግባብ የሙያ ክፍያ የተከፈላቸው መሆኑ ተረጋግጧል::

5. በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች በወጪ የተያዘ በድምሩ ብር 348,516.27 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ መገኘቱ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡
6. በበጀት ዓመቱ በወጪ ከተያዘው ሂሳብ ብር 4,396.50 በወጪ ያልተመዘገበ እንዲሁም ብር 3,765.90 በገቢ ያልተያዘ መገኘቱንና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ባለመመዝገቡ በበጀት ዓመቱ የወጪ እና የገቢ ሂሳብ ሪፖርቶች ያልተካተቱ መሆኑ፣
7. በባለሙያ ባልተረጋገጠ የክፍያ ምስክር ወረቀት በድምሩ ብር 4,414,048.24 ክፍያ መፈፀሙ፣
8. በድምሩ ብር 32,624,108.96 ውል የተገባባቸው የግንባታ ሥራዎች የህንፃ ስራ ተቋራጮቹ ከዩኒቨርሲቲው ጋር የነበረውን ውል ሲያቋርጡ ለአፈፃፀም የሚዘጋጅ የክፍያ ሠነድ (payment up on termination) ያላቀረቡ በመሆኑ የሥራ አፈፃፀሙንና የቀሪ ሥራውን መጠን ለመለየት አለመቻሉን፣
9. ለውሎ አበል የተከፈለ ብር 127,956.00 ወጪ ለመደረጉ በክፍያ ማወራረጃ ቅፅ ሠራተኛው ለጉዞ የተነሳበት እና የደረሰበት ሰዓት ባለመገለፁ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣

<u>**ተሰብሳቢ ሂሳብ፣**</u>

10. በሂሳብ መደብ 4210 ብር 293,250.00፣ በሂሳብ መደብ 4211 ብር 445,171.66 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4251 ብር 20,122,812.43 በድምሩ ብር 20,567,984.09 በተቀጽላ ሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ተመዝግቦ መገኘቱ፣
11. በሂሳብ መደብ 4201 በተሰብሳቢ የተያዘ በድምሩ ብር 229,478.30 በወቅቱ ሳያወራረድ ተገኝቷል፡፡

<u>**የተከፋይ ሂሳብ፣**</u>

12. በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 210,461.81 በተከፋይ ተይዞ መገኘቱን፣

<u>**የጉዳት ካሳ፣**</u>

13. ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ የህንፃ ሥራ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ በመከናወን ላይ የሚገኙት የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች በውላቸው መሠረት በወቅቱ ባለመጠናቀቃቸው ግንባታዎቹ ለዘገዩበት ተቋራጮች መክፈል የሚገባቸው በድምሩ ብር 759,069.39 የጉዳት ካሳ ገቢ አለመሰብሰቡ፣

<u>በጀት፣</u>

14.ከመደበኛ በጀት ብር 7,230,462.56 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 36,263,329.45 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ መደረጉን፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 14 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣</u>

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- በድምሩ ብር 7,459,377.57 ወጪ በተደረገባቸው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በየሂሳብ መደቦቹ ለተያዘው ወጪ በጀት መኖሩ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- በባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ክፍያ መፈጸም ሲገባው በድምሩ ብር 521,920.86 ከሳጥን ወጪ ሆኖ የተከፈለ መሆኑ፣
- በበጀት ዓመቱ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ ከመደበኛ በጀት ብር 7,452,485.48 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 150,817,205.05 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፣

<u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

- በዩኒቨርሲቲው የአላቂ ንብረት መጋዘን ለሚገኙ የተለያዩ እቃዎች ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመላቸው መሆኑን፣
- የሰሌዳ ቁጥሩ ኢት4-15934 ዳምባስ በብልሽት ምክንያት ለ4 ወራት ያለአገልግሎት ቁሞ የሚገኝ መሆኑ፣
- የ2 ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊቢሬዎች) አሽከርካሪዎች ሳያስረክቡ ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ መሆኑንና 1 ተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌለው መሆኑ፣
- በድምሩ ብር 62,706.85 ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች ሳይመልሱ ሠራተኞች ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ ለዩኒቨርሲቲው ሳይቀርብ የሠራተኛ ዝውውር የተፈፀመ መሆኑን፣
- ለዩኒቨርሲቲው በተፈቀደው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት 13 የኦዲት ባለሙያዎች መመደብ ሲገባቸው 5 የኦዲት ባለሙያዎች ብቻ በሥራ ላይ የሚገኙ በመሆኑ 8 የኦዲት ባለሙያዎች በቅጥር ወይም በዝውውር ያልተሟሉ መሆኑን፣

በ2008 ኦዲት ግኝቶች ላይ ስለተወሰደ የእርምት እርምጃ፣

ዩኒቨርሲቲው ለሚገነባቸው ህንፃዎች ከተለያዩ የህንፃ ስራ ተቋራጮች ጋር በገባው ውል መሰረት ግንባታዎቹ ባመጠናቀቃቸው መክፈል የሚገባው ብር 8,809,188.08 የጉዳት ካሣ ገቢ አለመደረጉን፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲውን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

  ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

  ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በአሶሳ ዩኒቨርስቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የዩኒቨርሲቲው የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፣</u>

1.1 <u>ግኝት፣ፈሰስ ያልተደረገ የውስጥ ገቢ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4 በራሳቸው የውስጥ ገቢ ዓመታዊ ወጪያቸውን እንዲሸፍኑ በአዋጅ የተፈቀደላቸው የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት ከተፈቀደላቸው በላይ ገንዘብ ከሰበሰቡ ተራፊውን ገንዘብ ወዲያውኑ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው ተደንግጓል። ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000021168355 በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2009 በቀረበው የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ የሚታይ ብር 6,627,408.44 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል።

1.2 <u>ስጋት፣</u>

የበጀት ዓመቱ ተራፊ ገቢ ፈሰስ ባለመደረጉ ለሌሎች መ/ቤቶች ሥራ እንዳይውል በዩኒቨርሲቲው ሥም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል።

1.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ፈሰስ ያልተደረገ ተራፊው ገንዘብ ለሚመለከተው አካል እንዲተላለፍ ዩኒቨርሲቲው ለባንኩ የማሳወቅ እና ተግባራዊ መደረጉን የመከታተል ኃላፊነት አለበት። በመሆኑም ገንዘቡ ፈሰስ እንዲደረግ ተገቢውን ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል።

1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

2.<u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

2.1 ግኝት፣ <u>ገቢ ያልተደረገ የጉዳት ካሣ፤</u>

የፌዴራል መንግስት ሰኔ/2002 ባወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 16፣17 ንዑስ አንቀፅ 16፣17፣4 (ሀ) መሠረት ውል የገባው አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውል መጠን ላይ 1/1ሺኛ የጉዳት ካሳ መክፈል እንደሚገባው እና የጉዳት ካሳ እንደሚከፍል ይገልፃል ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው የሚገነቡ ሕንጻዎች የግንባታ ሥራ አፈፃፀም ኦዲት ሲደረግ፤

ተስፋዬ አበበ ኮንስትራክሽን የስራ ተቋራጭ Dormitory DO (T2-TV-222 & DOT4 Mirr-220 የውል መጠን 14,288,773.00 የተሰራው ስራ 13,860,109.81 ያልተሰራ ስራ ብር 428,663.19 የዘገየበት ቀን ብዛት 243 ቀን (428,663.19*243*.001) የጉዳት ካሳ ብር 99,878.52 ያልከፈለ መሆኑ፣

ዮሴፍ ግርማይ ኮንስትራክሽን የስራ ተቋራጭ Dormitory DO (T2-TV-216 & DO-T4 -217 and washing basine (LN-T1-355) የውል መጠን 14,939,148.14 የተሰራው ስራ ብር 14,192,190.73፣ ያልተሰራ ስራ ብር 746,957.40 የዘገየበት ቀን ብዛት 196 ቀን (746,957.40*196*.001) የጉዳት ካሳ ብር 146,403.65 ያልከፈለ መሆኑ፣

ራዳር ኮንስትራክሽን የስራ ተቋራጭ Clinic (CL-502,dry Latrine DL (503,504,506,507,508 &509) administration lounge (AL-510) (T2-TV-222 & DOT4 Mirr-220 የውል መጠን 19,423,758.52 የተሰራው ስራ 16,315,957.15 ያልተሰራ ስራ ብር3,107,801.36 የዘገየበት የቀን ብዛት165 (3,107,801.36*165*.001) የጉዳት ካሳ ብር 512,787.22 ያልከፈለ ሲሆን፣

በድምሩ ብር 759,069.39 ከተቋራጮቹ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የጉዳት ካሳ ገቢ አለመደረጉ በኦዲቱ ተረጋግጧል። በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም በበጀት ዓመቴ ያልተሰበሰበው የጉዳት ካሣ ገቢ እንዲደረግ የማሻሻያ ሀሳብ ቢሰጥም እርምጃ አለመወሰዱ ታውቋል።

2.2 ስጋት፣

ውል የተገባባቸውና ከፍተኛ የካፒታል በጀት ወጪ የተደረገባቸው ግንባታዎች በወቅቱ አለመጠናቀቃቸው በተቋሙ የመማር ማስተማር ሂደት እና በሌሎችም አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ህንፃ መንግስት ላወጣው ወጪ ተመጣጣኝ ጥቅም እንዲያገኝ በገቡት ውል መሠረት ግዴታቸውን ያልተወጡ ተቋራጮች የጉዳት ካሣ መክፈል አለባቸው። ዩኒቨርሲቲው ግንባታዎቹ ተጠናቀው የተፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በስራ ተቋራጮች ላይ ጥብቅ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል።

2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3. የወጪ ሂሳብ፣

3.1.1 ግኝት፣ በጀት ስለመኖሩ በኃላፊ ሳይረጋገጥ የተፈፀመ ክፍያ፣

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 02 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ ለመቆጣጠር እንዲችል የበጀት መቆጣጠሪያ መዝገብ ወይም የተዘረጋ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት አመዘጋገብ ሊኖረው እንደሚገባ ያዛል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ 190/2002 ክፍል 3 ተራ ቁ 12 የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ነው፡፡ ሲሆን በዚሁ መሠረት ቁጥጥሩ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር 7,459,377.57 ወጪ በተደረገባቸው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በየሂሳብ መደቦቹ ለተያዘው ወጪ በጀት መኖሩ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ክፍያው የተፈጸመበት ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	14/02/09	71941	የባህር ዛፍ እንጨት ግዥ ክፍያ የተፈጸመበት	6244	124,122.95
2	1/13/09	71108	ለብረት ቧንቧ ግዥ ክፍያ የተፈጸመበት	6244	174,900.00
3	1/13/09	171109	ለሰንሰለት ግዥ ክፍያ የተፈጸመበት	6244	119,991.00
4	19/01/09	71717	ለብረት በሮች ግዥ	6244	35,300.00
5	18/01/09	71688	ለግምብ ድንጋይ ግዥ ክፍያ የተፈጸመበት	6244	93,270.00
6	18/01/09	71687	የአሸዋ ግዥ ክፍያ የተፈጸመበት	6244	140,784.00
7	19/07/09	0699503	ከኤን ኤም ኤች የኤሌትሪክና የውሃ ዕቃዎች የተገዘበት	6244	999,736.01
8	22/07/09	0699451	ለውሃ ጥገና ዕቃዎች ግዥ የተፈጸመበት	6244	101,924.94
9	20/07/09	0669505	የተማሪ ቀለብ ጥሬ ዕቃ ክፍያ የተፈጸመበት	6216	297,045.00
10	28/2/09	0698106	የዳቦ ዱቄት የተገዘበት የተፈጸመ	6216	308,309.76
11	04/04/09	71007	የተማሪ ቀለብ የተገዘበት የተከፈለ	6216	1,163,869.83
12	12/08/09	0699756	የመጋቢት ወር ደመወዝ የህንድ መምህራን ደመወዝ ክፍያ	6115	679,609.49
13	12/08/09	0699757	" "	6115	246,171.31
14	30/09/09	0699795	የግንቦት ወር የህንድ መምህራን ደመወዝ ክፍያ	6115	961,424.41
15	30/09/09	0699793	የግንቦት ወር የፕሮጀክት ሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ	6113	94,320
16	28/09/09	0699786	የሚያዚያ ወር የፕሮጀክት ሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ	6113	94,320
17	28/09/09	0699788	ከጥር-መጋቢት ወር የፕሮጀክት ሰራተኞች ደመወዝ	6113	51,228
18	27/03/09	323395/96	የህዳር ወር የፕሮጀክት ሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ	6113	85,074

19	11/09/09	0699250	ከበድሉ ባሴ የተማሪዎች ቀለብ ጤፍ፣ ቀይና ሽንኩርት ግዥ	6216	1,687,976.87
				ድምር	**7,459,377.57**

3.1.2 ስጋት፣

- ከተፈቀደ በጀት በላይ ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡
- መንግስት ያወጣውን ደንብና መመሪያ ያለመከተል ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል ፡፡

3.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፣

ወጪዎች ከመፈፀማቸው በፊት በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ኃላፊ መፈረሙ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡በተጨማሪም የበጀት አፈፃፀሙን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ማስተዳደር እንዲቻል ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.2.1 ግኝት፣በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች፣

የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች በወጪ የተያዘ በድምሩ ብር 348,516.27 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ መገኘቱ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል። ዝርዝሩ ቀርቧል።

ተራ ቁ	ቀን	የወጪው ምክንያት	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁ	የተመዘገበበት የሂሳብ መደብ	መመዝገብ የነበረበት የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	17/02/09	ተባይ ማጥፍያ ግዥ	1019219	6233	6221	49,075.00
2	07/02/09	ተባይ ማጥፍያ ግዥ	0715106	6214	6221	101,400.00
3	30/05/09	ለአጥር ሥራ የሚውል	0699007	6245	6244	198,041.27
					ድምር	348,516.27

3.2.2 ስጋት፣

- ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረገ የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ ላያሳይ ይችላል።
- የሂሳብ አያያዙ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።

3.2.3. የማሻሻያ ሀሳብ፣

ክፍያ እንዲፈጸም ከመደረጉ በፊት ለሂሳቦቹ በጀት መኖሩ መረጋገጡንና በጀት ከተያዘለት የሂሳብ መደብ መቀነሱንና በትክክለኛው የሂሳብ መደብ መመዝገቡን ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.3.1 ግኝት፣ አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 12 የመንግስት ሠራተኞች ደመወዝ ክፍያ አፈፃፀም እንደሚያዘው ለደመወዝ ዝግጅት መመሪያዎችመሟላት አለባቸው፡፡ የመ/ቤቱ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሠራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይህንንም መረጃ ወር በገባ በ20ኛው ቀን የፋይናንስ ተግባር ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ያሳውቃል፡፡ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ የተገለፀው ቢኖርም ሠራተኛው ከ20ኛው እስከ 30ኛወ ባሉት ቀናት በሥራ ላይ ካልተገኘ ተረጋግጦ ከዚያው ወር ደመወዙ ተመላሽ ይደረጋል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የደመወዝ አከፋፈል ሥርዐት መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በተለያዩ ምክንያቶች ሥራቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁ ሰራተኞች በሥራ ገበታቸው ላልተገኙባቸው ቀናት በድምሩ ብር 10,200.37 ተከፍሎ መገኘቱን፣
- በተለያየ ስሞች ወደ አንድ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ብር 18,590.26 የሠራተኞች ደመወዝ ገቢ መደረጉን፣
- ከሚከፈላቸው ደመወዝ በላይ በድምሩ ብር 1,635.58 ለ2 ሠራተኞች የተከፈለ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 30,426.21 አለአግባብ ለሠራተኞች ደመወዝ ተከፍሎ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተራ ቁ.	ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስከ	የሰራተኛው ስም	የለቀቁ በት ጊዜ	የወር ደመወዝ	መከፈል የነበረበት በወረዳ የውሎ አበል ተመን		ወደ አንድ የባንክ ሂሳብ ቁጥር	በብልጫ የተከፈለ
1	30/3/09	0700040	አኔና ነገሮ	19/3/0	2100	የ11	770.00		
2	30/3/09	0700040	አንተነህ በዘብህ	25/2/0	5081	የ30	4,011.60		
3	30/3/09	0700040	የሚያምረው በላይ	1/3/09	1586	የ30	1,096.38		
4	30/3/09	0700040	አጸደ ዘለቀ ገ/ስላሴ	12/3/0	1013	የ18	607.80		

5	30/3/09	0700040	አሳየ ጌትነት ሙላቱ	17/3/0	1511	የ13	654.70		
6	30/3/09	0700040	ታመነ ገብሩ	5/3/09	813	የ25	677.50		
7	30/3/09	0700040	ደስታ በቃና	16/3/0	961	የ1	352.36		
8	30/7/09	0699638	ታሪኬ ከበደቡልቻ	18/5/0	688	የ3	631.04		
9	30/7/09	0699638	ጠይባ መሀመድ	5/6/09		የ22	498.20		
10	30/7/09	0699638	አጸደ ዘለቀ ገ/ስላሴ	12/3/0	1,013	የ3	900.79		
11	30/3/09	0700040	አበበች ተሸመ		2,008	ህዳር/09		1708.74	
12	30/3/09	0700040	ደሳለኝ መለሰ		5,781	" "		4496.08	
13			አሸቴ ወልዴ		961	" "		857.63	
14	30/3/09	0700040	ሀብታም ደሴ		1,305	" "		1143.15	
15	30/3/09	0700040	ፀሀይ ብርሀኑ በርኼሶ		813	" ""			734.79
16	30/7/09	0699638	እሼቴ ወልዴ		961	የካቲት/		900.79	
17	30/7/09	0699638	ሀብታም ደሴ		1,305	" "		1,314.13	
18	3/8/09	0699491	አበበች ተሸመ		2,008	መጋቢ		1,708.74	
19	3/8/09	0699491	ደሳለኝ መለሰ		5781	" "		4,246.08	
20	3/8/09	0699491	እሼቴ ወልዴ		961			900.79	
21	3/8/09	0699491	ሀብታም ደሴ		1,305	" "		1,314.13	
22	3/8/09	0699491	ጌታቸው ታደሰ		1,013	" "			900.79
						ድምር	10,200.37	**18,590.26**	**1,635.58**

3.3.2 ስጋት፣

- የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- የዩኒቨርሲቲው በጀት ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡

3.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

አለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡በተለያዩ ሥሞች በአንድ የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገው ደመወዝ ተጣርቶ ለሚመለከተው ሠራተኛ እንዲከፈል መደረግ ይገባዋል፡፡ለወደፊቱም ክፍያዎች መመሪያን ተከትለው እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

3.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.4.1 ግኝት፣ መመሪያን ያልተከተለ የውሎ አበል ክፍያ፣

ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ.30/ጠ13/40/883 በቀን 29/10/2004 ባስተላለፈው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ መሠረት በተዘጋጀው የሂሳብ ማወራረጃ ቅፅ 2 ሂሳቡ እንዲወራረድ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ ለምርምር ስራ የውሎ አበል በድምሩ ብር 127,956.00 የተከፈለ ሲሆን፣ በክፍያ ማወራረጃ ሠራተኛው ለጉዞ የተነሳበት እና የደረሰበት

ሰዓት ባለመገለፁ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ አባሪ ተያይዟል፡፡

3.4.2 ስጋት፣

- መመሪያው ተግባራዊ አለመደረጉ ተጠያቂነትን ሊያመጣ ይችላል፡፡
- ተገቢው መረጃ ባለመቅረቡ ክፍያው በተመኑ መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

3.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጽም በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የውሎ አበል ክፍያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ዝርዝር መረጃ በቅፁ ላይ እንዲገለፅ እና በተገቢው የማወራረጃ ቅጽ እንዲወራረድ ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.5.1 ግኝት፣ አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣

መስከረም 8 ቀን 2002 የወጣው የውጭ አገር ጉዞ የውሎ አበል መጠን ለመወሰን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣ መመሪያ፤መሰረት ኦዲት ስደረግ ጋባዡ አገር ወይም ድርጅት ወጪ የሚሸፍን መሆኑን አስቀድሞ ያረጋገጠ በሚሆንበት ጊዜ ልዕካን ቡድኑ ከሙሉ ጥገኝነት ለማዳን ልዑኩ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የሆነው ሰንጠረዥ 2 የተመለከተውን የቀን አበል 30%(ሠላሳ በመቶ) እንደሚከፈለው መመሪያው ቢያመለክትም አቶ መሀመድ ኀበዜ ወደ ቻይና ሲጓዙ ወጪውን ጋባዡ አገር እንደሚሸፍን የተረጋገጠ ቢሆንም የሙሉ ቀን የቻይና አገር አበል በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 71414 ብር 17,446.68 እንዲሁም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 71526 ብር 28,350.00 በድምሩ ብር 45,796.68 በወጪ ተይዞ የተከፈለ ሲሆን መከፈል የነበረበት አበል (80ዶላር*21ቀን*30%*21.808)ብር10,991.232 እና ተጨማሪ የመልካም አገልግሎት ክፍያ (50 ዶላር*21.808) ብር 1090.40 በድምሩ ብር 12,081.632 በመሆኑ በብልጫ ብር 33,715.05 መከፈሉ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3.5.2 ስጋት፣

በመመሪያው መሠረት ክፍያ ባለመፈፀሙ የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ እና ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

3.5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከክፍያ ተመን በላይ ወጪ የተደረገው ገንዘብ ከሚመለከተው ሠራተኛ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም መመሪያን የተከተለ ክፍያ እንዲፈፀም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይገባዋል፡፡

3.5.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.6.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>አለአግባብ የተከፈለ የጥቅማ ጥቅም ክፍያ፣</u>

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችልና እስከ አሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማ ጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ አሳስቧል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፤ በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0058870 በሂሳብ መደብ 6251 በወጪ የተያዘ እና ለ3ኛው ሀገር አቀፍ ለምርምር ጉባኤ የወረቀት ጽሁፍ ላቀረቡ የሙያ ክፍያ ለእያንዳዳቸው ከብር 2,500.00 እስከ 5,000.00 በድምሩ ብር 95,900.00 አለአግባብ የተከፈላቸው መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡አባሪ ተያይዟል፡፡

3.6.2 <u>ስጋት፣</u>

መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ መፈፀሙ የመንግስት ገንዘብ እንዲባክን መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

3.6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ለተሳታፊዎች የተከፈለው የሙያ ክፍያ በመሆኑ እንደ ጥቅማ ጥቅም መታሰብ እንደማይገባው በመግለፅ ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም ተሳታፊዎቹ በጉባኤው ለመሳተፋቸው የተከፈላቸው የጥቅማ ጥቅም ክፍያ በመሆኑና የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ እንዲቆም እና በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ገንዘብ ወጪ እንዳይደረግ መመሪያው የሚያዝ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ እና ዩኒቨርሲቲው

በሚመለከተው አካል በማስፈቀድ ክፍያዎችን እንዲፈፅም ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

3.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲያችን ለ3ኛው ሃገር አቀፍ የምርምር ጉባዔ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን ላቀረቡ ባለሙያዎች ከብር 2,500.00 እስከ ብር 5,000.00 በድምሩ ብር 95,900.00 የተከፈለው እንደ ጥቅማጥቅም በማኔጅመንት ተወስኖ ተከፍሏል በሚል እንደ ግኝት ተደርጓል፡፡

1. ይህ ክፍያ የተፈጸመው እንደ ጥቅማ ጥቅም ሳይሆን ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅተው ለተሳታፊዎች ላቀረቡበት በጋራ የውል ስምምነት መሠረት አቅርበው ሲያጠናቅቁ እንደማንኛውም ክፍያ የመንግስት ግብር ተቀንሶ የተከፈለ የሙያ ክፍያ ነው፡፡
2. ማኔጅመንቱ ጥቅማ ጥቅምን ከመንግስት መመሪያ ውጭ በማኔጅመንት ወስኖ መክፈል እንደማይችል ያውቃል፡፡ ነገር ግን በማኔጅመንት ውሳኔ እንደ ጥቅማ ጥቅም ተወስኖ የተከፈለ ተደርጎ ነው የተያዘው እውነታው ግን ይህ አይደለም፡፡
3. አበል የተከፈላቸው የደርሶ መልስ የመንገድ ላይ ቆይታ እና የደርሶ መልስ የትራንስፖርት ብቻ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ይህ ዓይነት ክፍያዎች የማይቻል ከሆነ ግልጽ የሆነ መመሪያ እንዲሰጠን ምክንያቱም የሙያ ክፍያ መፈጸም እንደማይቻል ግልጽ የሆነ መመሪያ ባለማግኘታችን በሌላ መልኩ ደግሞ ለወደፊቱም በአሠራር ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ለማስተናገድ ስለምንቸገር ግልጽ የሆነ ማብራሪያ እንዲሰጠን እንጠይቃለን፡፡

3.6.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ዩኒቨርሲቲው ጥናታዊ ፁሁፍ ላቀረቡ ተሳታፊዎች የፈፀመው ክፍያ በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደ እና ለተለያዩ ባለሙያዎች የተለያየ ክፍያ በመፈፀሙ የክፍያ ተመኑን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ክፍያዎች በሚመለከተው አካል እንዲፈቀዱ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.7.1 ግኝት፣ አለአግባብ በጥሬ ገንዘብ የተፈፀመ ክፍያ፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 4 በተሻሻለው መመሪያ ‹‹የመንግስት መስሪያ ቤቶች እስከ ብር 5,000.00 የሚደርሱ

ወጪዎችን ቼክ መቁረጥ ሳያስፈልግ በገንዘብ ያዥ በኩል በጥሬ ገንዘብ መክፈል ይቻላል ይላል›› ይሁን እንጂ በጠቅላላ በድምሩ ብር የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ክፍያ መፈጸም ሲገባው ብር 521,920.86 ከሳጥን ወጪ ሆኖ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	ቀን	የወጪው ምክንያት	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	0715109	07/02/2009	ለተለያዩ መሣሪያዎች	6219	11,600.00
2	0712834	02/03/2009	ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች	6212	20,401.00
3	0715109	07/02/2010	ለፕላንትለማሽነሪ እና መሣሪያ መግዣ	6313	51,521.73
4	0715109	07/02/2010	ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች	6212	57,500.00
5	0715106	07/02/2010	ተባይ ማጥፊያ ግዥ	6214	101,400.00
6	0712834	07/02/2010	ለተለያዩ እቃዎች	6218	279,498.13
			ድምር		521,920.86

3.7.2 ስጋት፣

የጥሬ ገንዘብ በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ባለመጠበቁ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

3.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የመንግስት ገንዘብ የክፍያ አፈፃጸም መመሪያን ተከትሎ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.8.1 ግኝት፣በወጪ ማስመስከሪያ ሰነዶችና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ የተገኘ ልዩነት፣

ለመ/በቱ ከተፈቀደው በጀት ወጪ ሆኖ የተከፈለ እና በወጪ ማስመስከሪያዎች እና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች በወጪ የተያዘ ሂሳብ በአግባቡ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር በሂሳብ መደብ ብር 52,940.00 መመዝገብ ሲገባው 48,543.50 የተመዘገበ በመሆኑ ብር 4396.50 በወጪ ሳይመዘገብ መገኘቱን፣

- በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0714213 በሂሳብ መደብ 1101 ብር 17,303.10 መመዝገብ ሲገባው 13,537.20 የተመዘገበ በመሆኑ ብር 3765.90 በገቢ ሳይያዝ መገኘቱ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3.8.2 ስጋት፣

- የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል።
- የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል።

3.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በክፍያ ማስረጃዎች በወጪ እና በገቢ ደረሰኝ በገቢ የተያዘ ሂሳብ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ በአግባቡ እንዲመዘገብ እና በሂሳብ ሪፖርት እንዲካተት መደረግ ይኖርበታል።

3.8.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.9.1 ግኝት፣በአማካሪ መሐንዲስ ሳይረጋገጥ በቀረበ የክፍያ ምስክር ወረቀት የተፈፀመ ክፍያ፣

ሰኔ /2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 28.5 ፊደል ሀ መሰረት ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈጸመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲሱ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ እንደሆነ ይገልጻል። በተጨማሪም ከፍተኛ ዋጋ በሚጠይቁና ውስብስብ ወይም ቴክኒካል የሆኑ ስራዎች በሙያው በቂ ዕውቀት ያላቸው የውጭ አማካሪዎችን በመቅጠር ማሰራት እንደሚገባ በመመሪያው ተመልክቷል። ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ የህንፃ ተቋራጮች ጋር የኮብል ድንጋይ ማንጠፍ እና የተማሪዎች DSTV ግንባታ ሥራ በብር 5,171,426.02 ውል የገባ ሲሆን፣

- የማማከር ስራ በአማካሪ መሃንዲስ መከናወን ሲገባው በፕሮጀክት ጽ/ቤት ባለሙያው እንዲከናወን መደረጉን፣
- የክፍያ የምስክር ወረቀት በፕሮጀክት ጽ/ቤት ባለሙያው እንዲረጋገጥ እና ተዘጋጅቶ እንዲከፈል በመደረጉ፣

በድምሩ ብር 4,414,048.24 በባለሙያ ባልተረጋገጠ የክፍያ ምስክር ወረቀት ክፍያ መፈፀሙ ታውቋል፡፡

3.9.2 ስጋት፣

- መንግሥት ያወጣቸው አዋጅ፣ ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- ያለፈቃድ የማማከር አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ ለሚደርሰው የሥራ ግድፈት ተጠያቂነት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.9.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከፍተኛ በጀት የሚመደብለት የግንባታ ወጪ ተጠያቂነትን እና ኃላፊነትን ሊወስድ በሚችል አካል ክትትል ሊደረግለት የሚገባ በመሆኑ መመሪያን የተከተለ እሰራር ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.9.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲታያችን ይህን አማራጭ የተጠቀመው ፡-

- ያለ አማካሪ ወይም በፕሮጀክት መሃንዲሶች ቢሰራ ሊያስገኝ የሚችለውን የዋጋ ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት፡፡
- የኮብል ድንጋይ ንጣፍ ስራ ውስብስብ ባለመሆኑ እና በቀላሉ ማስተዳደር ስለሚቻል፣
- ስራዎቹ እንደ ደራሽ ስራ ስለሆኑ በቀላሉ ለመስራት፣
- ከፕሮጀክት ጽ/ቤት ውስጥ ያለው የሰው ሃይል ከበቂ በላይ የስራ ልምድ ያላቸው እና የተሟላ የሰው ሃይል ስላለ፣

3.9.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የግንባታ ሥራው በባለሙያ እንዲሰራ መደረጉ የሥራው ጥራት ክትትል እንዲደረግበት የሚያግዝ እና ተጠያቂነት የሚኖርበት ባለሙያ ኃላፊነቱን እንዲወስድ የሚያደርግ በመሆኑ በመመሪያው መሠረት ሊከናወን ይገባል፡፡

3.10.1 <u>ግኝት፣ የግንባታ ውል መቋረጡን እና የተከናወነውን ሥራ አፈፃፀም የሚገልፅ ሰነድ ያልቀረበለት፣</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ሀ) የመንግስት መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች የመስሪያ ቤታቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት በመወጣትና በመፈጸም በኩል መስሪያ ቤታቸውን ፕሮግራሞችና መስሪያ ቤታቸውን የሚመለከቱ ሕጎች በማስፈፀም በኩል ከፍተኛ ኃላፍነት እንዳለባቸው ይገልፃል። በዚሁ መሰረት በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ቦታዎች በመገንባት ላይ ያሉ ህንፃዎች በውላቸው መሠረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ።

- ርብቃ የስራ ተቋራጭ (phase 2 lot 6 SE-M2&DO-T4) የውል መጠን ብር 8,558,258.57 ከዩኒቨርሲቲው ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ ቢሆንም ውል በሚቋረጥበት ጊዜ ለአፈፃፀም የሚዘጋጅ የክፍያ ሠነድ (payment up on termination) ያልተሰራ መሆኑ፤
- ዘላለም አዱኛ የስራ ተቋራጭ (phase 2 lot 2 LAB-T2 133/135&SE-M2L-136) የውል መጠን ብር 21,201,500.62 phase 1B lot-4 Dormitory T2&T4የውል መጠን ብር 9,167,281.81 phase 1B lot-4 General story የውል መጠን ብር 2,255,326.53፣

በድምሩ ብር 32,624,108.96 ከዩኒቨርሲቲው ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ ቢሆንም ውል በሚቋረጥበት ጊዜ ለአፈፃፀም የሚዘጋጅ የክፍያ ሠነድ (payment up on termination) ያልተሰራ በመሆኑ የሥራ አፈፃፀሙንና ቀሪ ሥራውን መጠን ለመለየት አለመቻሉ ታውቋል።

3.10.2 <u>ስጋት፣</u>

የህንጻ ግንባታዎች በውላቸው መሰረት ካልተፈፀሙ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል።

3.10.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በውሉ መሰረት ያልፈፀሙ የስራ ተቋራጮች ከዩኒቨርሲቲው ጋር የገቡት ውል በሚቋረጥበት ወቅት ለአፈፃፀም የሚዘጋጅ የክፍያ ሠነድ እንዲዘጋጅ ማድረግ ይገባዋል። በተጨማሪም በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

3.10.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች (General condition of contract 22.1) ውል የተቋረጠው በስራ ተቋራጭ የውል መጣስ ከሆነ አማካሪ መሃንዲሱ በልዩ የውል ሁኔታዎች (Special condition of contract 22.1) በተገለጸው መሰረት የተከናወነው የግንባታ ስራ እና የታዘዙ የግንባታ ቁሶች ዋጋን በማሰብ የቅድመ ክፍያዎችን በልዩ የውል ሁኔታዎች መሰረት ላልተጠናቀቁ ስራ የሚቀነስ መቶኛ በመቀነስ ሰነድ ይዘጋጃል ተብሎ በተቀመጠ የውል አግባብ ግኝት ሆኖ ለቀረቡት ለሶስቱም ፕሮጀክቶች ውል ሲቋረጥ የሚፈጸም ክፍያ ተሰርቶ እንዲቀርብ ከዚህ በፊት የተደረገ ሲሆን ኤስ ጂ አማካሪ መሃንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሰርተው ያቀረቡት ክፍያ ያልተሰሩ ስራዎች ተጨምሮበት እና ተካትቶ ስለሆነ እና ሌሎች ችግሮች በሰነዱ ላይ ስለነበሩ ማስተካከያ ተደርጎ እንደገና እንዲሰራ ቢደረግም በተደጋጋሚ ተመሳሳይ ስህተት የክፍያ ሰነድ ሰርተው በአማካሪ ድርጅት በኩል ተረጋግጦ ሲቀርብ እንደነበረ፡፡

በወቅቱ የክፍያ ሰነዶች ላይ የነበሩ ስህተቶች ፡-

- ዘላለም አዱኛ ፌዝ ሁለት የላቦራቶሪ ጠረጴዛ የኤሌክትሪክ እና ሳኒተሪ እንስታሌሽን ሳይሰራ ክፍያ ውስጥ ተጠቃሎ ስለቀረቡ እንዲስተካከል የተደረገ መሆኑ፡፡
- ዘላለም አዱኛ ፌዝ አንድ ጀነራል ስቶር ውል ለተቋረጠው ፕሮጀክት የዋጋ ማስተካከያ ሰርተው ማቅረባቸው፡፡
- ለሶስቱም የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ለቀሪ ስራዎች የሚቆረጥ ቅጣት በትክክል ያልተሰላ መሆኑ፡፡
- የመያዣ (Retention) ክፍያ ሙሉ በሙሉ ለኮንትራክተሩ እንዲከፈል ተደርጎ ክፍያ ሰርቲፊኬት መሰራቱ፡፡

በእነኝህ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ክፍያው ተስተካክሎ እንዲቀርብ ቢደረግም በኤስ ጂ አማካሪ መሃንዲሶች በኩል ተረጋግጦ ስላልቀረበ ውል በሚቋረጥበት ጊዜ የሚዘጋጅ የክፍያ ሰነድ ፀድቆ ያልተጠቃለለ መሆኑን አቅርበናል፡፡

3.10.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ከተቋራጮች መቅረብ የሚገባው ዝርዝር መረጃ እንዲቀርብ፣ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ቅጣት እና ሌሎች ክፍያዎች በአማካሪ ባለሙያ በተረጋገጠ የክፍያ ምስክር ወረቀት መሠረት እንዲከፈሉ እንዲደረግ፣ እንዲሁም የቀሪ ሥረዎች ዝርዝር እንዲቀርብ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

4. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

4.1.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 4 ለ እና መ መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ይገልፃል እንዲሁም የተሰባሰቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንደአለበት መመሪያው ይገልፃል፡፡በዚሁ መሰረት የሚፈፀም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

በሂሳብ መደብ 4201 የተያዘ ከተለያዩ ሠራተኞች የሚፈለግ ብር 212,406.16 እንዲሁም ከጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የሚፈለግ ብር 17,072.14 በድምሩ ብር 229,478.30 በወቅቱ ሳያወራረድ ተገኝቷል፡፡

4.1.2 ስጋት፣

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል::

4.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

4.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

4.2.1 ግኝት፣ ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

የተሰባሳቢ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት ነሐሴ 1999 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መደብ 4210 የተያዘ ለመንግስት መ/ቤቶች የተሰጡ ሌሎች የቅድሚያ ክፍያዎች ብር 293,250.00፣ በሂሳብ መደብ 4211 የተያዘ ለግዥ ሠራተኛ ቅድሚያ ክፍያ ብር 445,171.66 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4251 የተያዘ ለሥራ ተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ ብር 20,122,812.43 በድምሩ ብር 20,861,234.09 በተቀጽላ ሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ተመዝግቦ መገኘቱ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

4.2.2 ስጋት፣

የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ካልተረጋገጠ የሂሳብ መገለጫዎቹ የዩኒቨርሲቲውን የፋይናንስ አቋም በትክክል ላይገልጹ ይችላሉ፡፡

4.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብ በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ ለወደፊትም የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው መረጋገጥ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል ለወደፊትም ሂሳባቸው ተጣርቶ አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

4.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በሂሣብ መደብ 4210 ተመዝግቦ የተገኘው ለመንግስት መ/ቤቶች ቅድመ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በወቅቱ ሲመዘገብ ወይም ክፍያው ሲፈጸም በተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተለትና ሂሳቡ ሲወራረድ በሌላ/በሁሴን ከድር/ የተቀጽላ ሌጀር ተመዝግቦ የተገኘው ሲሆን ምንም እንኳን የሂሳብ ሪፖርት አካል ባይሆንም ሪፖርትንም የማይነካ በመሆኑ በቀጣይ የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ የምናካሂድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በሂሣብ መደብ 4251 ለሥራ ተቋራጭ ኮንትራክተሮች የተከፈለ ቅድመ ክፍያ ብር 20,122,812.43 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን /በክሬዲት/ ተመዝግቦ የተገኘው ግኝት ስህተቱ የተፈጠረው በ2005 በጀት ዓመት በማንዋል ሲሰራ ስለነበረ እና በ2006 በጀት ዓመት ወደ IBEX ሲቀየር በአንድ የኮንትራክተር ስም በኦንሴት ኢንጅነሪንግ ተመዝግቦ የተገኘና በእያንዳንዱ የስራ ተቋራጭ ስም በተቀጽላ ሊጀር ያልተያዘ

በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ከፌደራል ገ/ኢ/ትብብር ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር በሕዳር ወር /2010 የማስተካከያ ምዝገባ በማካሄድ ያልተለመደው የሂሳብ ሚዛኑ የተስተካከለ መሆኑን እና የማስተካከያውን ደብዳቤ አያይዘን ያቀረብን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

4.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የማስተካከያ ምዝገባ መከናወኑ በተሰጠው ምላሽ ተገልፆ በተቀፅላ የሂሳብ ቋት መመዝገብ የሚገባው የተሰብሳቢ ሂሳብ ዝርዝር ቢቀርብም ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) የተመዘገበው ተሰብሳቢ ሂሳብ ማስተካከያ የተሰራለት ለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ፣

5.1 ግኝት፣

የዩኒቨርሲቲው የተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በሂሳብ መደብ 5004 የተያዘ ብር 37,887.00 የተጣራ የደመወዝ ተከፋይ የተከፋዩ ዕድሜና ለማን እንደሚከፈል ተለይቶ ያልተገለጸ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 5028 የተያዘ ብር 87,400.00 ለአካል ጉዳተኞች የሚከፈል ሲሆን፣ የተከፋዩ ዕድሜ ተለይቶ ያልታወቀ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 5054ሌሎች መያዣዎች ብር 85,174.81 ከጀደብ ኮንስትራክሽን ለትምህርት ሚኒስቴር መከፈል የሚገባው ከመስከረም/ 2006 ጀምሮ በተከፋይ የተያዘ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 210,461.81 በሰኔ 2009 የሂሳብ ሪፖርት በተከፋይ ተይዞ መገኘቱን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

5.2 ስጋት፣

- የተከፋይ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡
- የተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቶች ላይከፈሉ ይችላሉ፡፡

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተከፋይ ሂሳቡ ለማን እንደሚከፈልና መቼ በተከፋይ እንደተመዘገበ ለማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው የተያዙ ተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከተው አካል እንዲከፈሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

6. በጀት፣

6.1 ግኝት፣ ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት እና ከበጀት በላይ የወጣ፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ በየሂሳብ መደቦቹ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 7,452,485.48 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 150,817,205.05 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፣

ከመደበኛ በጀት ብር 7,230,462.56 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 36,263,329.45 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መደረጉን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

6.2 ስጋት፣

- የወጪ ሂሣብ በበጀት እቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡
- በበጀት ዓመቱ ተራፊ በጀት መገኘት በሌሎች መ/ቤቶች ሊሠራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡
- ከተፈቀደ በጀት በላይ ወጪ መደረጉ ዩኒቨርሲቲው ምንጩ ያልታወቀ ገቢ መሰብሰቡንና በአግባቡ ሪፖርት አለመደረጉን ሊያመለክት ይችላል፡፡

6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በበጀት ዓመቱ ሊከናወኑ የታቀዱ ግዥዎችና የተለያዩ ተግባራት ሊከናወኑ ባለመቻላቸው እና በተያዘው እቅድ መሠረት ሥራዎች ባለመሰራታቸው ያልተሰራበት የመደበኛና

የካፒታል በጀት ለመገኘቱ ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በእቅድ የያዛቸው ሥራዎች አለመሰራታቸው በጥናት ላይ ያልተመሰረተ እና የዩኒቨርሲቲውን የሥራ እንቅስቀቃሴ ያላገናዘበ እቅድ መዘጋጀቱን የሚያመለክት በመሆኑ በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ የበጀት እቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ አነስተኛ በጀት በመፈቀዱ ምክንያት በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከበጀት በላይ ወጪ መደረጉን በመግለፅ ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም ከበጀት በላይ ወጪ መደረጉ ዩኒቨርሲቲው ገቢውን በአግባቡ ሪፖርት አለማድረጉንና የተፈቀደለትን በጀት በአግባቡ አለመጠቀሙን የሚያመለክት በመሆኑ የሥራ አመራሩ ተገቢውን ማብራሪያ ሊስጥበት ይገባል፡፡ በመሆኑም በየወሩ በሥራ ክፍሉ በሚቀርበው የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት መሠረት ተራፊው በጀት በመ/ቤቱ ስም ተይዞ እንዳይቆይ በሌሎች መ/ቤቶች እንዲሰራበት ሪፖርት እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት እንዲጠቀም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- ያልተሰራበት የመደበኛ እና የካፒታል በጀትን በተመለከተ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የሥራ አመራሩ ተቀብሎታል፡፡
- <u>ስራ ላይ ያልዋለ የካፒታል በጀትን በተመለከተ</u>

  2009 በጀት ዓመት የተመደበው በጀት አዲስ ለሚገነቡ የአስተዳደር ህንጻዎችና የመምህራን መኖሪያ በጀት በጊዜው መጠቀም ባለመቻላችን የተፈጠረ እና በከፍተኛ ደረጃ ለግብአት ማሟያ ሲሆን በግዥ የሚከናወኑ የላብራቶሪ እቃዎች መማሪያ ሲሆን የግዥው ሂደት ውስብስብ በመሆኑና በበጀት ዓመቱ ውል የተገባም ቢሆን በገቡት ውል መሰረት ማቅረብ ባለመቻላቸው እና በችሮታ ጊዜም ምዝገባውን ብናካሂድም በበጀት ዓመቱ ክፍያውን መፈጸም ባለመቻላቸው የተፈቀደውን በጀት መጠቀም አልቻልንም ፡፡

- <u>ከበጀት በላይ ወጪ የሆነ የካፒታል በጀትን በተመለከተ</u>

  በ2009 በጀት ዓመት በግንቦት እና በሰኔ ወር 2009 በጀት ዓመት ፌደራል ገ/ኢ/ትብብር ሚኒስቴር በጀት ዝውውርም ሆነ የጥሬ ገንዘብ ፈላጎት ሊፈቅድልን ባለመቻሉ የተፈጠረ ሁኔታ በመሆኑና ለፌደራል ገ/ኢ. ትብብር ሚኒስቴር ማብራሪያ

የሰጠን ሲሆን በወቅቱ ዝውውር የታገደ በመሆኑ ምክንያት የተፈጠረ ስለሆነ ከጠቅላላው በጀት የማይበልጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

6.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በበጀት ዓመቱ ሊከናወኑ የሚገባቸው ግዥዎች በዕቅድ ተይዘው በወቅቱ የግዥ ሂደቱ ባለመጀመሩ አቅራቢዎች በበጀት ዓመቱ እንዳያቀርቡ ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡ በየሂሳቡ መደቡ ወጪ መደረግ የሚገባው ከተፈቀደው በጀት መብለጥ የማይገባው በመሆኑ በወቅቱ ዝውውር በመጠየቅ እና በመመሪያው መሠረት በጀትን በመጠቀም የተፈቀደለትን በጀት በሥራ ላይ ማዋል ይገባዋል፡፡

7.1 <u>ንብረት፣</u>

7.1.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፣አያያዝ እና አጠባበቅ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ፣ክፍል ሶስት አንቀጽ 9 ፊደል ተራ ሀ የስቶክ ቁጥጥር አስተማማኝ ተገቢና መሠረታዊ መዛግብቶችን መሠረት ያደረገ መሆን ያለበት መሆኑን የንብረት አጠቃቀምን አስመልክቶ የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገ ቢውን ሥርዓት መዘርጋት ያለበት መሆኑ የተገለጸ ሲሆን በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሠረት የዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በዩኒቨርሲቲው የአላቂ ንብረት መጋዘን ለሚገኙ የተለያዩ እቅዎች ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመላቸው መሆኑን፣
- የቋሚ ንብረት መጋዘን ጣሪያው በዝናብ ጊዜ የሚያፈስ በመሆኑ ዕቃዎች ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑን፣
- የተሰባበሩ የተማሪዎች መቀመጫዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ አለመደረጉንና በተቀመጡበት ግምጃ ቤት በአግባቡ እንዲያዙ አለመደረጉን፣

<u>የተሽከርካሪዎችን አያያዝ በተመለከተ፣</u>

- የሰሌዳ ቁጥሩ ኢት4-15934 ዳምባስ በብልሽት ምክንያት ለ4 ወራት ያለአገልግሎት ቆሞ የሚገኝ መሆኑ፣

- ሚኒባስ ኮዲ ኢት 4-15463፣ ዳዎ ኮዲ ኢት 4-15934 ኢት፣ ኒሳን መኪና ኮዲ ኢት 4-14414 መኪና ሊቢሬ (የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር) አሽከርካሪዎቹ ሳይመልሱ ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ መሆኑ፣
- ሰን ሎንግ ባስ ኮዲ ኢት 4-17012 ሊቢሬ (የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር) የሌለው መሆኑ፣
- ሰሎንግ አውቶቡሶች ኮድ ኢት 4-21904 እና ኢት 4-20476 ሊብሬው ላይ የሚገኘው የሞተር ቁጥር ከመኪናዎቹ ሞተር ጋር ሊናበብ/ሊገናኝ ያልተቻለ መሆኑ፣

7.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- ምዝገባው ባለመከናወኑ ምክንያት የንብረት ቁጥጥሩ የላላ እንዲሆን መንገድ ልከፍትና በመንግስት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለጥፋት ሊጋለጡ ይችላሉ።
- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ለተጨማሪ ብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ።
- የባለቤትነት መታወቂያ በተቋሙ ባለመገኘቱ ተሽከርካሪዎቹ የዩኒቨርሲቲው መሆናቸውን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል።

7.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ንብረቶቹ መንግስት ባወጣው መመሪያ መሠረት መጠበቅና እንክብካቤ ሊደረግለት ይገባል። ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ለሁሉም ንብረቶች እንዲከፈትላቸው መደረግ ይኖርበታል።እንዲሁም የተሽከርካሪዎቹ የባለበትነት መታወቂያ ደብተር እንዲወጣላቸው መደረግ አለበት የተሽከርካሪው ሞተር ቁጥር በባለሙያ ተጣርቶ ከሊብሬዎቹ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ሊጠገኑ ይገባል።

7.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

7.2.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>መ/ቤቱን ከለቀቁ ሠራተኞች ተመላሽ ያልተደረጉ ንብረቶ በተመለከተ፣</u>

ዩኒቨርሲቲውን የሚለቁ ሠራተኞች በእጃቸው የሚገኙ ንብረቶችን በአግባቡ ለመ/ቤቱ መመለሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በጠቅላላ በድምር ብር 62,706.85 ዋጋ

ያላቸውን ንብረቶች ሳይመልሱ ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ ሠራተኞች መኖሩ በኦዲት ተረጋግጧል። ዝርዝሩ በአባሪ ተያይዟል።

7.2.2 <u>ስጋት፣</u>

በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙትን ንብረቶች ለብክነት ሊጋለጡ ይችላል።

7.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የዩኒቨርሲቲውን ንብረት ሳይመልሱ ከዩኒቨርሲቲው የለቀቁ ሠራተኞች ንብረቱን እንዲመልሱ መደረግ ይኖርበታል።

7.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

8.1 <u>ልዩ ልዩ፣</u>

8.1.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ የማይደረግ መሆኑን በተመለከተ፣</u>

በመንግስት መ/ቤቶች ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር መዘርጋት የበላይ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት ሲሆን ስርዓቱም መ/ቤቱ ቀልጣፋ ጠንካራና ስኬታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ እንደሆነ ይታወቃል በመሆኑም፡- የመንግስት መ/ቤት ከተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማነት የተነሳ ወይም ስርዓቱ ባለመዘርጋቱ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለማስቀረት የስጋት ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን በግልጽ በመለየት በሰነድነት መያዝ እንዳለበት የገ/ኢ/ል/ሚር ያወጣው መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 13 ያዛል። ይሁን እንጂ በ2008 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት ወቅት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተደረገው ማጣራት፣ በ2009 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የተከታሰታልን ሲሆን አሁንም የተወሰደ እርምጃና በሰነድነት ተዘጋጅቶ የጸደቀ የሥጋት ተጋላጭነት ደሰሳ ጥናት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል።

8.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- መ/ቤቱ ለኦዲት ሪፖርት የሚሰጠውን ትኩረት ሊያሳንሰው ይችላል።
- በሪፖርት በሚሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት እርምጃ ያለመውሰድ ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል።

8.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩንቨርሲቲው የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ ለሥጋቶቹ የመፍትሔ አቅጣጫ በማስቀመጥ በሰነድነት መያዝና ሊሰራበት ይገባል፡፡

8.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

8.2.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ በሚመለከት፣</u>

የአስተዳደር ሰራተኞች አስተዳደራዊ መመሪያ ክፍል አራት የዝውውር አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 21.12.7 የዝውውር ደብዳቤ ከተዘጋጀ እና ከተሰጠ በኋላ የሰራተኛው ማህደር በዩኒቨርሲቲው መዝገብ ቤት ይጠበቃል ፡፡ ማህደሩም የሚከተሉትን ያካትታል፡፡ የሰው ሃይል ፍላጐት የተጠየቀበትና የፀደቀበት ቅፅ፣ የዝውውር ማስታወቂያ፣

በአመልካቹ ለመዛወር የተሞላ ፎርም የዝውውር ኮሚቴው ቃለ ጉባኤና የሃላፊ ውሳኔ፣ ልዩ ልዩ ማስረጃዎች የትምህርት ማስረጃ፣ የስራ ልምድ ማስረጃ መንጃ ፈቃድ ወ.ዘ.ተ…/ የስራ ውል የተፈረመበት ሰነድ፣ የስራ መደቡ የስራ ዝርዝር፣ እንዲሁም የዝውውር ደብዳቤው /ዋናውን ለመቀበሉ የፈረመበት ሆኖ፣ በማንኛውም ጊዜ ለሚነሱ አቤቱታዎችና ጥቆማዎች ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ የዝውውሩን ሂደት የሚያሳዩ መረጃዎች ቢያንስ ለ5 ዓመታት በሰው ሃብት መምሪያ የስራ ክፍል ተጠብቀው ሊቀመጡ ይገባል፡፡ ሆኖም መምህር በሪሁን ሙጨ ከ14/01/02 ጀምሮ በአክሱም ዩኒቨርሲቲ በቢዚነስ እና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ በመምህርነት ሙያ ያገለገሉ ሲሆን በቤተሰብ ችግር ምክንያት ወደ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ተዛውሮ ለመስራት ባቀረቡት ማመልከቻ በሚል አክስም ዩኒቨርሲት በ02/07/06 በደብዳቤ በጠየቀው መሰረት በቀን 9/11/05 በቁጥር ASU.PO 0049/05 በተጻፈ ደብዳቤ ከአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር ስምምነት ላይ በመድረስ ሰራተኛው በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ከቀን 1/7/2006 ጀምሮ የተዛወሩ ሲሆን፣

- በአክሱም ዩኒቨርሲቲ የተከፈተ የሰራተኛው የግል ማህደር በዝውውሩ ወቅት ያልመጣ እና አዲስ ማህደር በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የተከፈተ ሆኖ መገኘቱ፣
- ሰራተኛው ተዛውሮ ለመስራቱ ያቀረበው የማመልከቻ ደብዳቤ ለኦዲቱ አለመቅረቡን፣

- የትምህርት ማስረጃው አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ከተከፈተው የግል ማህደር ውስጥ ያልተገኘ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል ፡፡

8.2.2 <u>ስጋት፣</u>

- የመንግስትን መመሪያ ጠብቆ አለመስራት ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፤
- የመንግስትን መመሪያ ጥሰት ሊያስከከትል ይችላል ።

8.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ዝውውር ሲፈፀም ተፈላጊ የትምህርት፣ የስልጠና እንዲሁም የሥራ ልምድ መረጃዎች በእያንዳንዱ የሰራተኛ ማህደር እንዲጠበቁ መደረግ ይኖርበታል።

8.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

8.3.1 <u>ግኝት፣ የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ ኦዲት ክፍል በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት ፤ ዕውቀትና ክህሎት በላቸው ባለሙያዎች መደራጀት እንዳለበት ይገልፃል። በዚህ መሠረት የውስጥ ኦዲት አገልግሎት ጽ/ቤት የሰው ኃይልን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ፣ ለዩኒቨርሲቲው በተፈቀደው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት 13 የኦዲት ባለሙያዎች መመደብ ሲገባቸው በአሁን ሠዓት 5 የኦዲት ባለሙያዎች ብቻ በሥራ ላይ የሚገኙ በመሆኑ 8 የኦዲት ባለሙያዎች በቅጥር ያልተሟሉ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል።

8.3.2 <u>ስጋት፣</u>

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ተገቢው የሙያ ብቃት፤ ዕውቀትና ክህሎት በላቸው ባለሙያዎች ካልተደራጀ በዩኒቨርሲቲው የተዘረጋውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ጠንካራና ደካማ ጎኑን በመለየት ለዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር በተገቢው መንገድ ላይቀርብ ይችላል።

8.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የሥራ ክፍሉ የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይል እንዲሟላ ተገቢው ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

8.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

8.4.1 የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት አስተያየቶች ላይ እርምጃ አወሳሰድ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2016 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰረት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ 15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሰረት የዩኒቨርስቲው 2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ለሚገነባቸው ህንፃዎች ከተለያዩ የህንፃ ስራ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ ግንባታውን በውሉ መሰረት እንዲጠናቀቅ የውል ስምምነት ቢፈርምም ግንባታዎቹ 100 ቀናት እና ከ100 ቀናት በላይ ዘግይተው እየተጠናቀቁ ቢሆን ለዘገዩበት ቅጣት በውሉ ዋጋ ብር 88,091,880.80 ላይ 10% ተሰልቶ ብር 8,809,188.08 ለዘገየበት መክፈል ሲገባው ገቢ አለመደረጉን፣

8.4.2 ስጋት፣

- መ/ቤቱ ለኦዲት ሪፖርት የሚሰጠውን ትኩረት ሊያሳንሰው ይችላል፡፡
- በሪፖርት በሚሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት እርምጃ ያለመውሰድ ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡

8.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በዩኒቨርስቲው የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፍ ብሎም ግልፅኝነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡

8.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ይህ ግኝት የዘጠኝ ፕሮጀክቶች ግኝት ሲሆን ከእነዚህ መካከል አራት ፕሮጀክቶች (እያዩ ስብሃት ህ/ስ/ተ) በአማካሪ ድርጅት የተረጋገጠ የጊዜ ማራዘሚያ አቅርቦ

የፀደቀላቸው እና ከቅጣት ውጭ ሲሆን እንሴት ህ/ስ/ተ እና ይልማ ተረፈ ህ/ስ/ተ የተረጋገጠ እና የፀደቀ የጊዜ ማራዘሚያ የሌላቸው ሲሆን እስከ አሁን ክፍያ ባለማቅረባቸው ምክንያት ቅጣቱ ተግባራዊ አልተደረገምስለዚህ በዚህ አንጻሩም አልተቀመጡም የተባሉት ፕሮጀክቶች ጥቂቶች መሆናቸው እና የተረጋገጠ እና የፀደቀ ክፍያ ማየይኖራቸው ከሆነ በአማካሪ መሃንዲስ ተረጋግጦ በሚቀርብልን የክፍያ ሰነድ ይዘን በህግ አግባብ የምንጠይቃቸው ሆኖ ሌሎች ከቅጣት ውጭ ስለመሆናቸው አረጋግጠናል፣

8.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

የጊዜ ማራዘሚያ የተሰጣቸው ለመሆኑ ቢገለፅም በወቅቱ ከስራ ተቋራጮች ጥያቄው መቅረቡን የሚገልፅ መረጃ አልቀረበም፡፡ የጉዳት ካሣ የሚፈለግባቸው ተቋራጮች የክፍያ ምስክር ወረቀት በባለሙያ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ በማድረግ ከሚከፈላቸው ክፍያ ተቀናሽ በማድረግ የጉዳት ካሣው ገቢ እንዲደረግ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!